የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን

ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የፈቃድ ክፍያ መመሪያ ቁጥር----/2015

ግንቦት 2015

## የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የፈቃድ ክፍያን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ከኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ፣ ከሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ እና ከቁጥር አስተዳደር እና ምደባ እንዲሁም ከሬዲዮ ኮሙኒኬሽን እና ከቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት የሚሰበሰበውን የክፍያ መጠን በአግባቡ መወሰን በማስፈለጉ፤

ባለሥልጣኑ የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ መሰብሰብ የሚቻልበት መንገድ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ባለሥልጣኑ የሚሰበስባቸውን ክፍያዎች ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ግልጽ እና ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

ባለሥልጣኑ በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148 /2011 አንቀጽ 6(9) ፣ 6(20) ፣ 23 ፣ 26(1) ፣ 26 (2) ፣ 29 እና 54 (2) መሰረት ይህን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የፈቃድ ክፍያ መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የፈቃድ ክፍያ መመሪያ ቁጥር----/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ በአዋጁ እና በቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 792/2013 ላይ የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

2/ **"አስተዳደራዊ የማበረታቻ ዋጋ"** ማለት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ሃብት በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማበረታታት በባለሥልጣኑ ተግባራዊ የሚደረግ የዋጋ ተመን የማስቀመጥ ዘዴ ነው፤

3/ **"ባለሥልጣን"** ማለት በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 3 መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤

4/ **“ባንድ”** ማለት ተከታታይነት ያለው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አንድ ክፍል ነው፤

5/ **“ባንድዊድዝ”** ማለት በሬዲያ ፍሬኩዌንሲ ባንድ ወይም ቻናል ውስጥ የሚገኝ የስፔክትረም መጠን ወይም ስፋት ነው፤

6/ **“ቻናል”** ማለት መረጃን ለማስተላለፍ እና/ወይም ለመቀበል ጥቅም ላይ የሚውል የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ክፍል ነው፤

7/ **“መጨናነቅ ”** ማለት ቁጥራቸው የበዛ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ተጠቃሚዎች ተቀራራቢ ወይም አጎራባች የሆኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረምን በተመሳሳይ ግዜ ሲጠቀሙ የሚፈጠር ሁኔታ ነው፤

8/ **“ዱፕሌክስ ቻናል”** ማለት ኢንፎርሜሽን ለመቀበል እና ለመላክ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁለት የተለያዩ ፍሪኩዌንሲዎች ያሉት ቻናል ነው፤

9/ **“አዋጅ”** ማለት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ነው፤

10/ **“ከአንድ ማሰራጫ ወደ አንድ መቀበያ የሚደረግ ግንኙነት”** ማለት በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነው፤

11/ **“ከአንድ ማሰራጫ ወደ ብዙ መቀበያ የሚደረግ ግንኙነት”** ማለት ከአንድ ቋሚ ጣቢያ ወደ ብዙ ቋሚ ጣቢያዎች ወይም ተንቀሳቃሽ ተርሚናሎች የሚደረግ ግንኙነት ነው፤

12/ **“ስፔክትረም”** ማለት በ30 ኪሎ ኸርዝ እና በ300 ጊጋ ኸርዝ መካከል የሚገኝ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ነው፤

13/ **“የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ዋጋ”** ማለት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም የተወሰነ ክፍልን ለመጠቀም በየዓመቱ የሚከፈል ክፍያ ነው፤

14/ **“የስራ ቀናት”** ማለት ስራ የሚሰራባቸው ቀናት ሲሆን ቅዳሜ፣ እሁድ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ውስጥ የሕዝብ ባህላት ተብለው የተሰየሙ ቀናትን አይጨምርም፡፡

## 3. <u>አላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዋነኛ አላማ፡-

1/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና እድሳት ክፍያን መወሰን፤

2/ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያን መወሰን፤

3/ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮች ምደባ እና መጠቀሚያ ክፍያን መወሰን፣ እና

4/ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ምደባ እና የመጠቀሚያ ክፍያ በመወሰን ውጤታማ እና ኢኮኖሚዊ የሆነ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ባለሥልጣኑ በሚሰጣቸው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃዶች፣ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃዶች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ምደባ፣ የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. <u>አጠቃላይ መርሆች</u>

ባለሥልጣኑ፡-

1/ ከኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እንዲሁም ከሌሎች አገልግሎቶች የሚሰበሰበውን ክፍያ ያለአድልዎ ይሰበስባል፤

2/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የአገልግሎት ክፍያ መጠንን ለሕዝብ ግልጽ እና ተደራሽ ያደርጋል፤

3/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እንዲሁም የሌሎች ተያያዥ አገልግሎት ክፍያዎች ከሌሎች ተመጣጣኝ ገበያዎች ወይም ሃገራት ክፍያዎች ጋር የተቀራረቡመሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ</u>
### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
### <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ አተማመን ዘዴ</u>

6. <u>የክፍያ ዓይነቶች</u>

የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ የሚከተሉትን ክፍያዎች በነጠላ ወይም በአንድነት አካቶ ሊይዝ ይችላል፡-

1/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲን ለማስተዳደር የሚያወጣውን ወጪ ለመሸፍን በየዓመቱ የሚከፈል የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያን፤

2/ የተወሰነ የሬዲዮ ፍሬኩዌንሲ ክፍልን ለተወሰነ የፈቃድ ዘመን ወይም ጊዜ ይዞ ለመጠቀም የፍሪኩዌንሲ ፈቃዱ በሚሰጥበት ወቅት ወይም ባለሥልጣኑ በሚያስቀምጣቸው ሌሎች ጊዜያት የሚከፈል ክፍያን፤

7. <u>*የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ዋጋ መተመኛ መንገዶች*</u>

1/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ክፍያ እና የጨረታ መነሻ ዋጋን በሚወስንበት ወቅት እንደ ሁኔታው የሚከተሉትን የአሰራር ስርዓቶችን በተናጠል ወይም በጋራ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡-

ሀ) በጨረታ እንደገና ቢመደቡ ከፍተኛ ተፈላጊነት ሊኖራቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡ የነባር ወይም የተጨናነቁ ፍሪኩዌንሲዎች ምደባ ክፍያ አስተዳደራዊ የማበረታቻ ዋጋን መሰረት በማድረግ ይወሰናል፤

ለ) ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው ወይም መጨናነቅ ያለባቸው ባንዶች አዲስ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ምደባዎች ሲከናወኑ እንደ አስፈላጊነቱ ጨረታ ወይም ሌሎች በገበያ ላይ የተመሰረቱ ስልቶች ፍሪኩዌንሲን ለመመደብ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው:: ቀጣይነት ያለው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚ ክፍያ ወጪን ወይም አስተዳደራዊ የማበረታቻ ዋጋን መሰረት በማድረግ መወሰን አለበት::

ሐ) ከፍተኛ ተፈላጊነት ወይም መጨናነቅ በማይኖርበት ወቅት፤ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አስተዳደር ማበራታቻ ዋጋን እና/ወይም ባለሥልጣኑ ፍሪኩዌንሲን ለማስተዳደር የሚያወጣውን ወጪ መሰረት በማድረግ ዓመታዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ብቻ እንዲከፈልባቸው ይደረጋል፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ክፍያ እና የጨረታ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚከተሉትን ዘዴዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤

ሀ) በሌሎች ሀገሮች ወይም ገበያዎች የሚከፈሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያዎችን በመውሰድ ንጽጽር ማድረግ እና በገበያ ሁኔታዎች ላይ የሚታዩ ልዩነቶች የማስተካከያ ሁኔታዎች በመጠቀም ፣ እና

ለ) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ባለቤቶች ገቢ እና የወጪ ሁኔታዎችን በመገመት፡፡

8. <u>መረጃ ስለመሰብሰብ እና የክፍያ ሁኔታዎች አፈጻጸም</u>

1/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያን ለመወሰን የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የሚከተሉትን መረጃዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ከሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ተጠቃሚዎች ይሰበስባል፤

ሀ) የማስተላለፊያ ወይም የተርሚናሎች ብዛት፤

ለ) የማስተላለፊያዎች ወይም የተርሚናሎች መገኛ ቦታ፤

ሐ) በእያንዳንዱ ማስተላለፊያ ወይም ተርሚናል ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ ፍሪኩዌንሲዎች ወይም ቻናሎች፤

መ) እያንዳንዱ ማስተላለፊያ ወይም ተርሚናል የሚጠቀመው ባንድዊድዝ፤ እና

ሠ) ሌሎች አስፈላጊ ዳታዎች፡፡

2/ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲተጠቃሚዎች በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 1 የተመለከቱ መረጃዎችን ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡለት በጠየቀ በአስር (10) የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡፤

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አገልግሎት ክፍያዎች</u>

9. <u>ለሞባይል ፍሪኩዌንሲ</u>

ለሞባይል አገልግሎት ለተመደቡ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች የሚከፈለው ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ በሚከተለው ዝርዝር መሠረት ይሆናል፡-

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | ዓመታዊ የአገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያ (የአሜሪካ ዶላር/በሜጋ ኸርዝ/በዓመት) |
|---|---|
| 450 ሜጋ ኸርዝ | 23,911.00 |
| 600 ሜጋ ኸርዝ | 77,330.70 |
| 700 ሜጋ ኸርዝ | 70,265.60 |

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | ዓመታዊ የአገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያ (የአሜሪካ ዶላር/በሜጋ ኸርዝ/በዓመት) |
|---|---|
| 800 ሜጋ ኸርዝ | 84,395.80 |
| 900 ሜጋ ኸርዝ | 76,597.40 |
| 1800 ሜጋ ኸርዝ | 41,611.40 |
| 2100 ሜጋ ኸርዝ | 41,295.80 |
| 2600 ሜጋ ኸርዝ | 7,195.00 |
| 3500 ሜጋ ኸርዝ | 3,935.00 |

10.<u>በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት ለተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች</u>

በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት ለተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች የሚከፈለው ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ በሚከተለው መልክ የሚሰላ ይሆናል፦

**ክፍያ =ለእያንዳንዱ 2 X 1 ሜጋ ኸርዝ ሊንክ** = መነሻ ዋጋ X የባንድ ሁኔታ X ባንድዊድዝ

መነሻ ዋጋ = 62.84 የአሜሪካ ዶላር

**የባንድ ሁኔታ**

- 1 ጊጋ ኸርዝ እና ከ1 ጊጋ ኸርዝ በታች = 0.5
- ከ1 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 10 ጊጋ ኸርዝ = 1
- ከ10 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 20 ጊጋ ኸርዝ = 0.75
- ከ20 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 30 ጊጋ ኸርዝ = 0.25
- ከ30 ጊጋ ኸርዝ በላይ = 0.1

## 11.<u>በቋሚ ጣቢያና ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት ለተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች</u>

በቋሚ ጣቢያና ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት ለተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች የሚከፈለው ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሰርት የሚሰላ ይሆናል፡-

- **ክፍያ= ለእያንዳንዱ ኔትዎርክ** = መነሻ ዋጋ X የባንድ ሁኔታ X ባንድዊድዝ X ኔትዎርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ X የቦታ ሁኔታ
- **መነሻ ዋጋ** = 62.84 የአሜሪካ ዶላር
- **የባንድ ሁኔታ**
    - 1 ጊጋ ኸርዝ እና ከ1 ጊጋ ኸርዝ በታች = 0.5
    - ከ1 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 10 ጊጋ ኸርዝ = 1
    - ከ10 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 20 ጊጋ ኸርዝ = 0.75
    - ከ20 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 30 ጊጋ ኸርዝ = 0.25
    - ከ30 ጊጋ ኸርዝ በላይ = 0.1
- **የቦታ ሁኔታ**
    - ከተማ=1
    - ገጠር=0.5
- ኔትዎርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ

| የሚሸፈነው ክልል | ኔትዎርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ |
|---|---|
| የሚሸፍነው ክልል, ≤ 5 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 1 |
| የሚሸፍነው ክልል, > 5 ኪሎ ሜትር ስኩዌር እና ≤ 600 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 2 |
| የሚሸፍነው ክልል, > 600 ኪሎ ሜትር ስኩዌር እና ≤ 1,200 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 3 |
| የሚሸፍነው ክልል, > 1,200 ኪሎ ሜትር | 10 |

| የሚሸፈነው ክልል | ኔትዎርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ |
|---|---|
| ስኩዌር እና ≤ 500,000 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | |
| የሚሸፍነው ክልል, > 500,000 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 30 |

## 12.ለብሮድካስት አገልግሎት ለሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች

ለብሮድካስት አገልግሎት ለሚውሉ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች የሚከፈለው ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ በሚከተለው ዝርዝር መሠረት ይሆናል፡-

| የማሰራጫ አይነት | | ከተማ/የአሜሪካ ዶላር/በእያንዳንዱ ማሰራጫ | ገጠር/የአሜሪካ ዶላር/በእያንዳንዱ ማሰራጫ |
|---|---|---|---|
| አጭርና መካከለኛ ሞገድ | የግል/የንግድ | 500 | |
| | የማህበረሰብ/የህዝብ | 250 | |
| ኤፍ ኤም (የማሰራጫ ጉልበት <= 1 ኪሎ ዋት) | የግል/የንግድ | 500 | 250 |
| | የማህበረሰብ/የህዝብ | 250 | 175 |
| ኤፍ ኤም (የማሰራጫ ጉልበት > 1ኪሎ ዋት) | የግል/የንግድ | 700 | 350 |
| | የማህበረሰብ/የህዝብ | 350 | 175 |
| ቴሌቪዥን (የማሰራጫ ጉልበት <= 1Kw) | የግል/የንግድ | 954 | 750 |
| | የማህበረሰብ/የህዝብ | 800 | 600 |
| ቴሌቪዥን (የማሰራጫ ጉልበት> 1Kw) | የግል/የንግድ | 1500 | 1300 |
| | የማህበረሰብ/የህዝብ | 1000 | 800 |

## 13.ለመገናኛ ሬድዮ አገልግሎት ለሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች

1/ ለመደበኛ የመገናኛ ሬድዮ ፍሪኩዌንሲ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሰርት የሚሰላ ይሆናል፡-

- **አመታዊ የፍሪኩዌንሲ ክፍያ** = መነሻ ዋጋ X የሽፋን ሁኔታ X የባንድ ዊድዝ ሁኔታ X የሬድዮኖች ብዛት ሁኔታ
- **መነሻ ዋጋ** = 20 የአሜሪካ ዶላር
- **የሽፋን ሁኔታ**

| የሽፋን መግለጫ | የሽፋን ሁኔታ |
|---|---|
| እስከ 15 ኪ.ሜ ለሚደርስ ሽፋን | 1 |
| እስከ 30 ኪ.ሜ ለሚደርስ ሽፋን | 2.5 |
| እስከ 60 ኪ.ሜ ለሚደርስ ሽዕፋን | 5 |
| ሀገራዊ ሽፋን ላለው | 15 |

- **የባንድ ዊድዝ ሁኔታ**

| የተመደበ ባንድ ዊድዝ | ባንድዊድዝ ሁኔታ |
|---|---|
| 3 ኪሎ ኸርዝ ወይም 6.25 ኪሎ ኸርዝ ወይም 12.5 ኪሎ ኸርዝ ወይም 20 ኪሎ ኸርዝ ሲምፕሌክስ ቻናል | 1 |
| 3 ኪሎ ኸርዝ ወይም 6.25 ኪሎ ኸርዝ ወይም 12.5 ኪሎ ኸርዝ ወይም 20 ኪሎ ኸርዝ ዱፕሌክስ ቻናል | 2 |
| 25 ኪሎ ኸርዝ ሲምፕሌክስ ቻናል | 1.25 |
| 25 ኪሎ ኸርዝ ዱፕሌክስ ቻናል | 2.5 |

➢ **የሬድዮኖች ቁጥር ሁኔታ**

| የሬድዮኖች ቁጥር | የሬዲዮኖች ሁኔታ |
|---|---|
| እስከ 10 ሬድዮኖች | 1 |
| ከ 11 እስክ 35 ሬድዮኖች | 2 |
| ከ 35 ሬድዮኖች በላይ | 3 |
| ለሀገራዊ ሽፋን ፍሪኩዌንሲው/ዎቹ በብቸኝነት ሲመደብ/ቡ | 4 |

2/ የግል ወይም የህዝብ ትራንክ ኔትዎርክ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሰርት የሚሰላ ይሆናል፡-

➢ **ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ ክፍያ** = መነሻ ዋጋ X የሬድዮኖች ቁጥር ሁኔታ X የግል ወይም የህዝብ ሁኔታ

➢ **መነሻ ዋጋ** = 10 የአሜሪካ ዶላር

➢ የግል ወይም የህዝብ ሁኔታ

ለግል = 1

ለህዝብ = 0.5

## 14.ለኤሮናቲካል እና ለማሪታይም አገልግሎት ለሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች

ለኤሮናቲካል እና ማሪታይም አገልግሎት ለሚውል ፍሪኩዌንሲ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሰርት የሚሰላ ይሆናል፡-

➢ **ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ ክፍያ = መነሻ ዋጋ X ባንድ ዊድዝ ሁኔታ**

➢ **መነሻ ዋጋ = 20 የአሜሪካ ዶላር**

➢ **የባንድ ዊድዝ ሁኔታ**

| የተመደበ ባንድ ዊድዝ | ባንድዊድዝ ሁኔታ |
|---|---|
| 6.25 ኪሎ ኸርዝ ወይም 12.5 ኪሎ ኸርዝ | 2 |
| 25 ኪሎ ኸርዝ | 2.5 |

## ክፍል ሦስት

## የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ እና የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ

15.የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት ለሚሰጠው የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ያስከፍላል፡፡

2/ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ወይም የሚመረቱ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ብዛት ከአንድ በላይ ቢሆንም ለተመሳሳይ ሞዴሎች የሚከፈለው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ ለአንዱ መሳሪያ የሚከፈለው የክፍያ መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

3/ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ወይመ የሚመረቱ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ሞዴል የተለያየ ከሆነ ለቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚከፈለው ክፍያ በእያንዳንዱ የተለያዩ ሞዴሎች ሆኖ ለአንዱ መሳሪያ የሚከፈለው ክፍያ ይሆናል፡፡

16.የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ መጠን

1/ ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚከተሉትን ክፍያዎች ያስከፍላል፡፡

| ቁጥር | የመሳሪያው ስም | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለግለሰብ መጠቀሚያ) (በአሜሪካ ዶላር) | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለተቋም እና ለንግድ ድርጅት) (በአሜሪካ ዶላር) |
|---|---|---|---|
| 1 | የተርሚናል መሳሪያዎች | | |
| | • መደበኛ ስልክ (ባለገመድ/ገመድ አልባ)<br>• የሞባይል ቀፎ<br>• የፋክስ ማሽኖች | 2 | 30 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • የሲዲኤምኤ ገመድ አልባ የስልክ ቀፎ<br>• የአይፒ ስልኮች<br>• አይፓድ/ታብሌት<br>• ብሉቱዝ ሞጁል እና የዋይፋይ ሞጁል ያለው ላፕቶፕ<br>• የሞባይል ዋይፋይ ራውተሮች<br>• 3G/4G/5G የሞባይል መጠቀሚያ USB Dongle<br>• ፖስ ማሽን<br>• የሳተላይት ሞባይል ስልኮች እና<br>• ሌሎች መሰል መሳሪያዎች | | |
| 2 | አነስተኛ ኃይል/ጉልበት ያላቸው መሣሪያዎች (የአጭር ርቀት መሣሪያዎች) | | |
| | • ዋይ ፋይ፣ ብሉቱዝ ሞጁሎች<br>• የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መለያ መሳሪያዎች<br>• ቴሌሜትሪ እና የትእዛዝ ሞጁሎች<br>• ገመድ አልባ ማይክሮፎኖች<br>• የርቀት ቁልፍ አልባ የመግቢያ እና ተደራሽነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች<br>• ተሽከርካሪ እንዳይንቀሳቀስ ማድረጊያ መሳሪያ<br>• የእንቅስቃሴ መከታተያ መሳሪያ<br>• ገመድ አልባ ማንቂያ ሲስተም<br>• የገመድ አልባ የአካባቢ ኔትዎርክ መዳረሻ ነጥብ<br>• የገመድ አልባ የአካባቢ ኔትዎርክ ሞጁል/ ካርዶች<br>• በሰው አካል ላይ ወይም ውስጥ ተገጥመው ድጋፍ የሚሰጡየሕክምና መሳሪዎች እና<br>• ሌሎች መሰል መሳሪያዎች | 2 | 20 |
| 3 | የጥሪ ማዞሪያ መሣሪያዎች/የግል ቅርንጫፍ ማዞሪያ መሳሪያዎች | | |
| | • እስከ 16 የሚደርሱ የውስጥ መሰመሮች | አይፈቀድም | 25 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • ከ 16 በላይ እስከ 32 የውስጥ መስመሮች | አይፈቀድም | 50 |
| | • ከ 32 በላይ እስከ 64 የውስጥ መስመሮች | አይፈቀድም | 75 |
| | • ከ 64 በላይ እስከ 128 የውስጥ መስመሮች | አይፈቀድም | 100 |
| | • ከ128 በላይ እስከ 256 የውስጥ መስመሮች | አይፈቀድም | 150 |
| | • ከ256 በላይ የውስጥ መስሮች | አይፈቀድም | 200 |
| 4 | የአይቲ ኔትዎርክ መሳሪያዎች | | |
| | • ሞደም፣ ስዊች፣ ራውተር፣ ሰርቨር እና መሰል መሳሪያዎች | 30 | 50 |
| 5 | የሞባይል ሬዲዮ እና ዋና የኔትዎርክ መሳሪያ | | |
| | • BSCs፣ MSCs፣ BTS፣ Node B፣ eNodeB፣ gNodeB (gNB)፣ ማይክሮዌቭ ሬዲዮ፣ ኮር ስዊች፣ ጌትዌይ እና መሰል መሳሪያዎች | አይፈቀድም | 900 |
| 6 | የሬዲዮ መገናኛ መሳሪያዎች | | |
| 6.1 | • ኤችኤፍ፣ ቪኤችኤፍ፣ ዩኤችኤፍ ሬዲዮ<br>• ከአንድ ማሰራጫ ወደ ብዙ መቀበያ የሚያሰራጭ ሬዲዮ ከአንድ ማሰራጫ ወደ አንድ መቀበያ የሚያሰራጭ ሬዲዮ | አይፈቀድም | 100 |
| 6.2 | • አማተር ሬዲዮ/የሲቲዝን ባንድ ሬዲዮ እና<br>• ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች | 10 | 50 |
| 7 | የምድር የሳተላይት ተርሚናል | | |
| | • ቪሳት<br>• የሳተላይት ሞደም<br>• የሳተላይት ራውተር እና<br>• ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች | አይፈቀድም | 100 |

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ የሚከፈል ክፍያ

### 17. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ እና በቴሌኮሙኒኬሽን ፍቃድ መመሪያ ቁጥር 792/2013 መሰረት ለሚሰጠው ፈቃድ ተገቢውን የፈቃድ እና የእድሳት ክፍያ ያስከፍላል፤

2/ ፈቃዱ የጠፋበት፣ የተበላሸበት፣ ወይም በሌላ ምክንያት ፈቃዱ እንዲተካለት የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለባስልጣኑ በማቅረብ እና ለዛ ፈቃድ የተቀመጠውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈል ምትክ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀበት ምክንያት ባለሥልጣኑ በፈጸመው ስህተት ከሆነ እርማት ለማድረግ ወይም ምትክ ፈቃድ ለመስጠት ባለፈቃዱ ክፍያ እንዲፈጽም አይጠየቅም፡፡

### 18. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ መጠን

1/ ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ የሚከተሉትን ክፍያዎች የሚያስከፍል ይሆናል፤

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን አገልግሎቱ ስም | የማመልከቻ ክፍያ ( የአሜሪካ ዶላር) | የፈቃድ ክፍያ ( የአሜሪካ ዶላር) | ዓመታዊ አስተዳደራዊ ክፍያ | የፈቃድ ዘመን (በአመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 500 | 100,000 | 1% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 10 ዓመት |
| 2 | የዳታ ማዕከል አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 500 | 10,000 | 1% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 10 ዓመት |
| 3 | የሆስቲንግ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 500 | 2,500 | 0.5% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 5 ዓመት |
| 4 | የጥሪ ማዕከል አገልግሎት ፈቃድ፤ | 500 | 10,000 | 0.5% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 5 ዓመት |
| 5 | የቴሌኮሙኒኬሽን ተጨማሪ አገልግሎቶች ፈቃድ፤ | 100 | 1,500 | $ 500 (በአሜሪካ ዶላር) | 5 ዓመት |

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን አገልግሎቱ ስም | የማመልከቻ ክፍያ ( የአሜሪካ ዶላር) | የፈቃድ ክፍያ ( የአሜሪካ ዶላር) | ዓመታዊ አስተዳደራዊ ክፍያ | የፈቃድ ዘመን (በአመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የመሠረተልማት አቅርቦትን ያላካተተ የኢንተርኔት አገልግሎት አቅርቦት ፈቃድ፤ | 500 | 5,000 | 0.5% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 3 ዓመት |
| 7 | ዓለም አቀፍ የሳተላይት የግል ሞባይል ግንኙነት አገልግሎት ፈቃድ፤ | 500 | 5,000 | $ 5,000 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |
| 8 | የግል ኔትዎርክ እና እርስበርስ የተያያዘ የተጠቃሚች ግሩፕ | 500 | 3,000 | $ 3,000 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |
| 9 | የውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ፤ | 50 | 300 | $ 200 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |
| 10 | የውጭ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ፤ | 500 | 2,5000 | $ 2,5000 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |
| 11 | ብሔራዊ የፖስታ አገልግሎት ፈቃድ | 1,000 | 50,000 | 0.2% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 15 ዓመት |
| 12 | ዓለም አቀፍ የፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት ፈቃድ | 200 | 5,000 | 0.4% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 1 ዓመት |
| 13 | ሃገር አቀፍ የፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት | 200 | 1,000 | $ 1000 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |

## 19.<u>የሳተላይት እና የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ፈቃድ</u>

ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው የሳተላይት እና የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ፈቃድ የሚከተሉትን ክፍያዎች የሚያስከፍል ይሆናል፡፡

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን መሳሪያ ስም | መለኪያ | የፈቃድ ክፍያ (በአሜሪካ ዶላር) | የእድሳት ክፍያ (በአሜሪካ ዶላር) |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቪሳት መሣሪያ ፈቃድ | በመሣሪያ ብዛት | 20,000 | 20,000 |
| 2 | የግል የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃድ | በመሣሪያ ብዛት | አይከፈልበትም | አይከፈልበትም |

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ክፍያ

### 20.የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር የክፍያ ዓይነት እና መጠን

1. ባለሥልጣኑ ለሚመድበው የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር የምደባ እና ዓመታዊ ክፍያ የሚያስከፍል ይሆናል፤
2. ባለሥልጣኑ የምደባ እና ዓመታዊ ክፍያ የሚያስከፍለው ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡-

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት (በአሜሪካ ዶላር)/ | ዓመታዊ ክፍያ/ በተመደበ የቁጥር ብዛት/ በአሜሪካ ዶላር) |
|---|---|---|---|
| 1 | ለመደበኛ፣ ለሞባይል፣ ከማሽን ወደ ማሽን አይኦቲን ጨምሮ እና ለቮይስ ኦቨር አይፒ አገልግሎት የሚውሉ ቁጥሮች | 0.03 | 0.03 |
| 2 | ብሔራዊ የሲግናሊንግ ፖይንት ኮድ (SPC) | 1,000 | 1,000 |
| 3 | ዓለም አቀፍ የሲግናሊን ፓይንት ኮድ (ISPC) | 3,000 | 3,000 |
| 4 | የሞባይል ኔትዎርክ ኮድ (ኤምኤንሲ) | 3,000 | 3,000 |
| 5 | የኔትዎርክ ቀለም ኮዶች (ኤን.ሲ.ሲ.) | 200 | 200 |
| 6 | የሰጪ መለያ ቁጥሮች (IIN)/ሲም ሄደር | 200 | 200 |
| 7 | የዳታ ኔትዎርክ መለያ ኮዶች (DNIC) | 200 | 200 |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት (በአሜሪካ ዶላር)/ | ዓመታዊ ክፍያ/ በተመደበ የቁጥር ብዛት/ በአሜሪካ ዶላር) |
|---|---|---|---|
| 8 | የአገልግሎት አቅራቢ ምርጫ/የቅድመ ምርጫ ኮዶች | 1,000 | 1,000 |
| 9 | **ዩኤስኤስዲ ኮዶች** | | |
| 9.1 | 3 ዲጂት ዩኤስ ኤስ ዲ ኮዶች (ምሳሌ*123#) | 300 | 300 |
| 9.2 | 4 ዲጂት ዩኤስ ኤስ ዲ ኮዶች (ምሳሌ*123*4#) | 150 | 150 |
| 9.3 | 5 ዲጂት ዩኤስ ኤስ ዲ ኮዶች እና ከዛ በላይ (ምሳሌ*123*45#) | 75 | 75 |
| 10 | **ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ አጭር ቁጥሮች** | | |
| 10.1 | **ፕላቲኒየም**<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 5 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 44444)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 5 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 23456)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 4444)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 2345)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 444)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተከታታይ አሃዞች (ለምሳሌ 234) | 50 | 2,000 |
| 10.2 | **ወርቅ**<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 1 4444)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 7 1234) | 50 | 1,000 |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት (በአሜሪካ ዶላር)/ | ዓመታዊ ክፍያ/ በተመደበ የቁጥር ብዛት/ በአሜሪካ ዶላር) |
|---|---|---|---|
| | • ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 2 ጥንድ ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 11 444)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 2 ጥንዶች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 1 34 34፣ 1 22 55)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁትር ሆኖ 2 ጥንዶች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 34 34)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ ጥንድ ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 22 55)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (2 456)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 2 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 3 44) | | |
| 10.3 | **ብር**<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 13 444)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተደጋጋሚ አሃዞች (ለምሳሌ 3444)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ በተመሳሳይ አሃዝ የሚጀምር እና የሚያልቅ እና ጥንድ ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 3443፣ 5005)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ በተመሳሳይ አሃዝ የሚጀምሩ እና የሚያልቁ ቁጥሮች (ለምሳሌ 343፣ 505) | 50 | 800 |
| 10.4 | **ነሐስ**<br>• ከላይ የተገለጹት ምድቦች ላይ የማይካተቱ ባለ 5፣ 4 እና 3 አሃዝ አጭር ቁጥሮች | 50 | 600 |
| 11 | የድንገተኛ እና የደህንነት አገልግሎቶች ቁጥሮች (ፖሊስ, | ነጻ | ነጻ |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት (በአሜሪካ ዶላር)/ | ዓመታዊ ክፍያ/ በተመደበ የቁጥር ብዛት/ በአሜሪካ ዶላር) |
|---|---|---|---|
| | የእሳት አደጋ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶች, የልጅ እርዳታ መስመር) | | |
| 12 | ለደንበኛ አገልግሎት እና ለሂሳብ አከፋፈል ተዛማጅ ጥያቄዎች ባለ 3-አሃዝ የተለመዱ የኔትዎርክ መረብ ኮዶች | ነጻ | ነጻ |
| 13 | የቁጥር ማዛወር ቅድመ-ቅጥያ ኮዶች/ የቁጥር ማዛወር የራውቲንግ ኮዶች (NPRC) | ነጻ | ነጻ |
| 14 | ማህበራዊ፣ ሰብአዊ እና ህዝባዊ አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ለመንግስት አገልግሎት የተመደቡ ቁጥሮች:: | ነጻ | ነጻ |

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21.የክፍያ ጊዜ

1/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት መከፈል አለበት::

2/ ዓመታዊ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ዕድሳት ክፍያ በኢትዮጵያ መንግስት በጀት ዓመት በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሣሥ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ ፈቃድ ሲታደስ መከፈል አለበት::

3/ የሳተላይት እና የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃድ ክፍያ  ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ መከፈል አለበት::

4/ የሳተላይት እና የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃድ ዕድሳት ክፍያ በኢትዮጵያ መንግስት በጀት ዓመት በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ ፈቃድ ሲታደስ መከፈል አለበት::

5/ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ ክፍያ ፍሪኩዌንሲ በሚመደብበት ወቅት መከፈል አለበት፡፡

6/ ዓመታዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መጠቀሚያ ክፍያ በኢትዮጵያ መንግስት በጀት ዓመት በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ መከፈል አለበት፡፡

7/ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ምደባ ክፍያ ቁጥሩ በሚመደብበት ወቅት መከፈል አለበት፡፡

8/ ዓመታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር መጠቀሚያ ክፍያ በኢትዮጵያ መንግስት በጀት ዓመት በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ መከፈል አለበት፡፡

9/ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት በሚሰጥበት ወቅት መከፈል አለበት፡፡

## 22. ክፍያ የሚፈጸምበት ሁኔታ

1/ በዚህ መመሪያ የተደነገጉት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የፈቃድ ክፍያዎች ተመን በአሜሪካ ዶላር የተቀመጡ ቢሆንም ክፍያው ባለሥልጣኑ ኢንቮይስ በሚያዘጋጅበት ቀን የሚኖረውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጣ የእለት የምንዛሪ ተመን ተጠቅሞ በማስላት ተዘጋጅቶ በሚቀርበው የክፍያ መጠየቂያ ኢንቮይስ ላይ በሚገለጸው መሠረት በብር የሚፈጸም ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቪሳት፣ የዓለም አቀፍ የሳተላይት የግል ሞባይል ግንኙነት አገልግሎት ፈቃድ እና የግል ኔትዎርክ እና እርስበርስ የሚገናኙ የተጠቃሚዎች ግሩፕ ፈቃድ አመልካች ወይም ባለፈቃድ ዓለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ወይም ኤምባሲ ወይም የውጭ ሀገር ኩባንያ ከሆነ የፈቃድ እና የዕድሳት ክፍያ መጠየቂያ ኢንቮይስ በአሜሪካ ዶላር ተዘጋጅቶ ክፍያውም በቀጥታ በአሜሪካ ዶላር የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 23.ቅጣት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 ንዑስ-አንቀጽ (2) ላይ በተጠቀሰው የፈቃድ ማሳደሻ ጊዜ ውስጥ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃድ ፈቃዱን ካላሳደሰ ከጥር 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ላለው ጊዜ ከፈቃድ ማሳደሻው በተጨማሪ ፈቃድ ማሳደሱ ለዘገየበት ለጥር ወር ብር 2,500 ብር (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) እና ለሚቀጥለው እያንዳንዱ

ወር ብር 1,500 ብር (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ቅጣት በመክፈል ፈቃዱን ያሳድሳል፡፡

2/ በቅጣት የማደሻ ጊዜ ውስጥ ያላደሰ ማንኛውም የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃድ በቅጣት የማደሻው ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከፈቃድ ማሳደሻው በተጨማሪ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) በመክፈል ማሳደስ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ያልታደሰ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ያንኑ ፈቃድ መልሶ ማውጣት የሚቻለው በቅጣት የማሳደሻ ጊዜው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ያለምንም ተጨማሪ ቅጣት እንደ አዲስ ፈቃድ መውሰድ ይቻላል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (6) እና (8) ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ተገቢውን የሳተላይት እና የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃድ ዕድሳት፣ ዓመታዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መጠቀሚያ፣ ዓመታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር መጠቀሚያ እንዲሁም ማንኛውንም አስተዳደራዊ ክፍያ ያልከፈለ ማንኛውም ሰው የሚከተለው የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡-

ሀ) ለመጀመሪያው አንድ ወራት የአጠቃላይ ክፍያው 1%፤

ለ) ለሁለተኛው ወር የአጠቃላይ ክፍያው 2%፤

ሐ) ለሶስተኛው ወር የአጠቃላይ ክፍያው 5% እንዲከፈል ይደረጋል፤

መ) ባለፍቃዱ ከሶስት (3) ወራት በላይ ፈቃዱን ሳያሳድስ ወይም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እና የቁጥር መጠቀሚያ ክፍያውን ሳይፈጽም ከቀረ፤ ባለስልጣኑ ፈቃዱን እንደ ሁኔታው ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፤

## 24.<u>የተሻሩ ህጎች</u>

1/ የቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 1/1997 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ የግል ቪሳት ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 6 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 25.ማሻሻያ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለሁሉም ባለፈቃዶች በቅድሚያ በማሳወቅ እና ከአዋጁ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የባለድርሻ አካላት የምክክር ሂደት በማካሄድ በማንኛውም ጊዜ ይህን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

## 26.መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ----ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ --- ቀን 2015 ዓ.ም**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**
**የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**